የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፮
አዲስ አበባ — ኅዳር ፲፱ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 6
ADDIS ABABA – 28th November, 1996

ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፱ Investment Incentives (Amendment) Council of Ministers Regulations No. 9/1996.
የኢትዮጵያ ቴሌኮሙ... የኢንቨስትመንት ማበረታቻ(ማሻሻያ) የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር 9/1989.
የሚኒስትሮች ምክር ...

CONTENTS

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲/ ፲፱፻፺፱
የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽንን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬/፲፱፻፹፯ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፭፭/፲፱፻፹፰ በአንቀጽ ፵፯/፩/ሀ/ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፲/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· መቋቋም

፩· የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን (ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽኑ" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ።

፪· ኮርፖሬሽኑ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፭፭/፲፱፻፹፰ መሠረት ይተዳደራል ።

COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS No. 10/1996
COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF THE ETHIOPIAN TELECOMMUNICATION CORPORATION

These Regulations are issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 4/1995 and Article 47(1) (a) of the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

   These Regulations may be cited as the "Ethiopian Telecommunication Corporation Establishment Council of Ministers Regulations No. 10/1996."

2. *Establishment*

   1. The Ethiopian Telecommunication Corporation (hereinafter "the Corporation") is hereby established as a public enterprise.
   2. The Corporation shall be governed by the public Enterprises Proclamation No.25/1992.

ያንዱ ዋጋ Unit Price 1·30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

በመንግሥት የሚሰየም አካል የኮርፖሬሽኑ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ይሆናል ።

፬· ዋና መሥሪያ ቤት

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ሊኖረው ይችላል ።

፭· ዓላማ

ኮርፖሬሽኑ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው ፤

፩· የመንግሥትን የልማት ፖሊሲና ቅድሚያ ትኩረት መሠረት በማድረግ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን ማቋቋም ፣ ማካሄድ ፣ መጠገንና ማስፋፋት ፤

፪· የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ የቴሌፎን ፣ የቴሌክስ ፣ የቴሌ ፋክስ እና ሌሎች የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን መስጠት ፤

፫· የቴሌቪዥን ፕሮግራሞችን ተቀብሎ ማስተላለፍን ጨምሮ በተቀናጀ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የሚሰጡ የኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን መስጠት፤

፬· የቴሌኮሙኒኬሽንና ተዛማጅ መሣሪያዎችን መጠገን ፣ መገጣጠምና ማምረት ፤

፭· ለቴሌኮሙኒኬሽን ባለሙያዎች የሥልጠና አገልግሎት መስጠት ፤

፮· ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ የሆኑ ሥራዎችን ማካሄድ ።

፮· ካፒታል

ለኮርፖሬሽኑ የተፈቀደለት ካፒታል ብር ፩ቢሊዮን ፬፻፸፫ ሚሊዮን ፱፻፹ ሺህ ፭፻፸፰ (አንድ ቢሊዮን አራት መቶ ሰባ ሦስት ሚሊዮን ዘጠኝ መቶ ሰማንያ ሺህ አምስት መቶ ሰባ ስምንት ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፬፻፹ ሚሊዮን ፬፻፶፱ ሺህ ፭፻፸፰ (አራት መቶ ሰማንያ ሚሊዮን አራት መቶ ሃምሳ ዘጠኝ ሺህ አምስት መቶ ሰባ ስምንት ብር) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል ።

፯· ኃላፊነት

ኮርፖሬሽኑ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በእዳ ተጠያቂ አይሆንም።

፰· ኮርፖሬሽኑ የሚቆይበት ጊዜ

ኮርፖሬሽኑ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ።

፱· የመብትና ግዴታ መተላለፍ

በአዋጅ ቁጥር ፭፻፴፭/፲፱፻፺፭ መሠረት ይተዳደር የነበረው የቀድሞው የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ባለሥልጣን መብትና ግዴታዎች በዚህ ደንብ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል።

፲· ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኅዳር ፲፱ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም·

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

3. *Supervising Authority*

A body to be designated by the Government shall be the supervising authority of the Corporation.

4. *Head Office*

The Corporation shall have its head office in Addis Ababa and may have branch offices elsewhere as may be necessary.

5. *Purposes*

The purposes for which the Corporation is established are:

1) to engage, in accordance with development policies and priorities of the Government, in the construction, operation, maintenance and expansion of telecommunication services;

2) to provide domestic and international telephone, telex, telefax and other communication services;

3) to provide communication services using integrated information technology, including re-broadcasting of television broadcasts;

4) to repair, assemble and manufacture telecommunication equipment and ancillaries;

5) to render training services to telecommunication personnel;

6) to engage in other related activities necessary for the attainment of its purposes.

6. *Capital*

The authorized capital of the Corporation is Birr 1,473,980,578 (one billion four hundred seventy three million nine hundred eighty thousand and five hundred seventy eight Birr) of which Birr 480,459,578 (four hundred eighty million four hundred fifty nine thousand and five hundred seventy eight Birr) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Corporation shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Corporation is established for an indefinite duration.

9. *Transfer of Rights and Obligations*

The rights and obligations of the former Ethiopian Telecommunication Authority operated under Proclamation No. 131/1952 are hereby transferred to the Corporation.

10. *Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of their publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 28th day of November, 1996

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ ።
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE